OFFICE OF THE STATE
SUPERINTENDENT OF EDUCATION

**ለ፦** ጭማሪ የማይደረግለነት የልጆች እክብክካቤ አገልግሎት ሰጪዎች እና የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች ክፍያ ኢኩዊቲ ፈንድ

**ከ፦** ሳራ ሜያድ
የኤርሊ ቻይልድሁድ ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ

**የሚከተለውን በሚመለከት፥** ለ2024 በጀት አመት (FY24) የኤርሊ ቻይልድ ሁድ የአስተማሪዎች ክፍያ ኢኩዊቲ ፈንድ ኮሎምቢያ ዲስትሪክት አገልግሎት ሰጪ ስምምነት ላይ የተደረገውን ለውጥ ማሳወቂያ

**ቀን፦** ኦገስት 19, 2024

---

የግዛቱ የትምህርት ሱፐርኢንቴንደንት ቢሮ (OSSE) የ2024 በጀት አመትን (FY24) የአገልግሎት ሰጪ ስምምነትን ለኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ የክፍያ ኢኩዊቲ ፈንድ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ እያዘመ እና እያስተካከለ ነው፤ ይህም የሚከናወነው ክፍል XIII (የስምምነት ጊዘ) እና ክፍል XV (የስምምነት ማስተካከያ) መሰረት ለFY25 ኤርሊ ቻይልድ ሁድ አስተማሪዎች ክፍያ ኢኩዊቲ ፈንድ አቅራቢዎች ሽፋን ነው አገልግሎት ሰጪዎች የስምምነት ማሰተካከያውን ሞልተው መፈረም ያለባቸው ሲሆን ይህም ከስር በተቀመጠው መመሪያ መሰረት በኤርሊ ቻይልድ ሁድ የአስተማሪዎች ክፍያ ኢኩዊቲ ፈንድ ውስጥ FY25 ላይ ተሳትፎ ለማድረግ ነው።

## I. የስምምነትን ማሻሻያ

OSSE የሚከተሉትን የማስተካከያ ማሳወቂያዎች በጽሁፍ እያቀረበ ሲሆን ይህም ለኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች ክፍያ ኢኩዊቲ ፈንድ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ነው፦

- OSSE የFY24ን ክፍል XIII (የስምምነት ጊዜ) እያስተካከለ ነው ይህም ለኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ክፍያ ኢኩወቲ ፈንድ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የአገልግሎት ስምምነት ሲሆን “Sept. 30, 2024” የሚለውን ሀረግ በማጥፋት እና “Sept. 30, 2025” በሚለው በመተካት ነው።
- OSSE ሁሉም አገልግሎት ሰጪዎች በFY24 የአገልግሎት ሰጪ ስምምነት ውስጥ ያለውን ክፍል XVIII እንዲያዘምኑ ይጠይቃል። በዚህ የአገልግሎት ማተካከያ ላይ አንድ ጊዜ ከዘመነ በኋላ የተከፋዩ መረጃ በዚህ ክፍል ውስጥ የቀረበው መረጃ ሁሉ የሚበልጥ ይሆናል ማለት ነው።
- በክፍል XV (የአገልግሎት) ማተካከያ መሰረት ሁሉም ወገኖች አብሮ የተያያዘውን የውል ማስተካከያ መፈረም አለባቸው።
- OSSE “ECE salary scale for Fiscal Year 2024 (FY24)” የሚለውን ሀረግ በማጥፋት እና “ECE salary schedule for Fiscal Year 2025 (FY25) published by OSSE” በሚለው በመተካት ስምምነቱን እያስተካከለው ነው።
- OSSE ክፍል I.A.5 “ለእያንዳንዱ የልጆች እድገት ተቋም ጥቅም ላይ የሚውለው የCDF የደሞዝ መክፈያ ቀመር የሚሰላው በOSSE የተቀመጠውን የፈንድ ቀመር በመጠቀም ሲሆን ይህም በኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ኢኩዊተብል ክፍያ ግብረ ሀይል በተጠቆመው መሰረት እና የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ኢኩዊቲ ፈንድን ስልጣን በሰጠው አዋጅ መሰረት በዲሲ አዋጅ ላይ ባለው መሰረት እያንዳንዱ የሩብ አመት ክፍያ በሚሰላበት ጊዜ ነው። የተቋሚ የሩብ አመት CDF ደሞዝ

መክፈያ የሚከተሉት ድምር ለአራት ሲካፈል ይሆናል፦

a. የተቋሙ መሠረት ሽልማት፣ በ I.B ውስጥ የተገለጸውን ስሌት በመጠቀም እንደተወሰነው
b. የተቋሙ አስተዳደራዊ ማጎልበቻ፣ በ I.C ውስጥ የተገለጸውን ስሌት በመጠቀም እንደተወሰነው
c. የተቋሙ የፍትሃዊነት ማስተካከያ፣ የሚመለከተው ከሆነ፣ በ I.D ውስጥ የተገለጸውን ስሌት በመጠቀም እንደተወሰነው

- OSSE I.B.1.dን ሰርዞታል፦ “የድጋፍ አድራጊ አስተማሪዎችን ቁጥር (በ DC Code §4-401 ላይ በተገለጠው መሰረት)
- OSSE ክፍል I.B.2 “የFY25 የደሞዝ ጭማሪ መጠኖች በሚና እና ማእረግ በOSSE ላይ ከተቀመጠው መጠን ጋር በእያንዳንዱ የሩብ አመት ክፍያ የሚኖረውን የደሞዝ ጭማሪ መጠኖች ያንጸባርቃል” ብሎ እንዲነበብ አስተካክሏል።
- OSSE የክፍል I.B.2 ንኡስ አንቀጽ መ (“ማንኛውም የCDA ድጋፍ አድራጊ አስተማሪ መምህር ጭማሪ: $2,329”) ን በማጥፋት እና ንኡስ አንቀጾች ሰ እና ረን እንደ መ እና ሰ እንዲነበቡ በማድረግ ማስተካከያ አድርጓል።
- OSSE ክፍል I.B.2. ላይ የሚከተሉትን ርእሶች በመጨመር ማስተካከያ አድርጎበታል፦ “የአስተማሪዎች የደሞዝ ደጎማ” እና “የድጋፍ አድራጊ አስተማሪዎች ደሞዝ ጭማሪ።"
- OSSE ክፍል I.C ላይ “15 በመቶ” የሚለውን በማጥፋት እና “የአስተዳደር መቶኛ ክፍልፋይ በእያንዳንዱ ሩብ አመት ክፍያ ላይ በOSSE በተጻፈው መሰረት” በሚል ተክቶታል።
- OSSE ክፍል I.D “የእያንዳንዱ ፋሲሊቲ ኢኩዊቲ ማስተካከያ የሚሰላው በOSSE የታተመመውን የኢኩዊቲ ማስሊያ ቀመር በእያንዳንዱ የሩብ አመት ክፍያ በመጠቀም ነው” ተብሎ እንዲነበብ በማድረግ ማስተካከያ አድርጓል።
- OSSE ክፍል I.Eን በማጥፋት ማስተካከያ አድርጓል፦ የFY24 ጭማሪ
- OSSE ክፍል V.B.1.c ላይ “DELLT ላይ ስቀል” የሚለውን ሀረግ “OSSE በሚመክረው መድረክ በኩል አስገቡ” በሚል ሀረግ በመተካት ማስተካከያ አድርጓል።
- OSSEክፍል XXIV ወደ “የምስልር ወረቀት” እየቀየረው እና የሚከተለውን ቋንቋ እየጨመረው ነው፦ የFY24 ኤርሊ ቻይልድሁድ የክፍያ ኢኩዊቲ ፈንድ ስምምነት በሚተገበርበት ጊዜ ለOSSE ያቀርብኳቸው ሰነዶች በሙሉ ጊዜያዊ እና ያልተለወጡ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ። እነዚያ ሰነዶች የቀጣሪ መታወቂያ ቁጥርን (EIN)፣ ከዲስትሪክት ጋር ቅንጅት ያለውን የፋይናንስ ሲስተም (DIFS) ምዝገባ፣ W-9 መረጃ እና ስልጣን ያለው ወኪል ቅጽን የሚያካትት ነው።
- OSSE ክፍል XXIVን XXV ብሎ ቀይሮታል። የዚህ ክፍል “ፊርማዎች” የሚለው ርእስ እንደዛው ነው። OSSE የሚከተለውን ሀረግ ሰርዞታል፦ “DUNS ቁጥር” ከዚያም “SAM UEI ቁጥር” እና “SAM የአገልግሎት ማብቂያ ቀን” በሚለው ተክቶታል ሁሉም አገልግሎት ሰጪዎች ለሽልማት አስተዳደር (SAM) ሲስተም ንቁ የሆነ ልዩ የተቋም መለያ (UEI) ማረጋገጥ አለባቸው።

## II. አስፈላጊ ሰነዶች

OSSE EIN፣ DIFS ምዝገባ እና አሁን ላይ በየኤርሊ ትምህርት ፈቃድ መሳሪያ ክፍል (DELLT)፣ እና በኮክስ ሊንክ በኩል የቀረበውን ስልጣን ያለው ወኪል ቅጽ የተሰቀለውን W-9 መረጃ መጠቀም ይቀጥላል። ባለፈው አመት ላይ የተደረገ ምንም አይነት ለውጥ ያለ እንደሆነ ለOSSE.ECEPayEquity@dc.gov ኢሜይል በመላክ OSSEን ያሳውቁት። ምንም

አይነት ለውጥ ያልተደረገ እንደሆነ የ FY25 ሰነድ ላይ ምንም ለውጥ እንዳልተደረገ ለማሳየት በማስተካከያው ስምምነት ውስጥ ያለው ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ።